ቀን፡ ሚያዚያ 8/2004 ዓ.ም

<u>በፋሲካ ሌሊት በጉራ ፋርዳ የተፈናቃይ ሰባት ቤቶች በካድሬዎች መቃጠላቸውን የሚገልጽ መረጃ</u>

<u>መኢአድ ደረሰው፡፡</u>

**ከአዲስ አበባ ወደ ጉራ ፋርዳ የጉበ 5 ተፈናቃዮች በቁጥጥር ሥር ውለዋል፡፡**

**ካድሬዎች እስካሁን 3,000 የአማራ ተወላጆች ማፈናቀላቸውን አመኑ፡፡**

በደቡብ ኢትዮጵያ በቤንቺ ማጂ ዞን በጉራ ፋርዳ ወረዳ ሚያዚያ 6 ለ 7 / 2004 ዓ.ም. አጥቢያ የፋሲካ ሌሊት ከአዲስ ዓለም ማርያም ሠፈር በስተጀርባ ገርጂ ከሚባለው ሠፈር ተፈናቅለው ከአካባቢው የተሰደዱ የአማራ ተወላጅ የሆኑ ሰባት ቤቶች ከነሙሉ ዕቃቸው በካድሬዎች በእሳት መጋየታቸውን የዓይን እማኞች ለመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ገለጹ፡፡

የተቃጠሉት ቤቶች ባለቤቶች የሆኑ አባወራዎች ብዙዎቹ ተሰደው አዲስ አበባ ያሉ መሆናቸውና ቤተሰቦቻቸው ግን ጉራ ፋርዳ ወረዳ ውስጥ በየዘመዱ ቤት ተጠግተው ያሉ መሆናቸው ታውቋል፡፡ ተፈናቅለው የነበሩት ሰዎች ጉራ ፋርዳ ሊመለሱ ይችሉ ይሆናል የሚል ጉምጉምታ በመሰማቱ ሲመለሱ የሚገቡበት ቤት ለማሳጣት የተደረገ የሹማምንቱ ዕኩይ ተግባር መሆኑንም የዓይን ምስክሮች ይናገራሉ፡፡

በጉራፋርዳ የቀሩት የአማራ ተወላጆች የፋሲካ ሌሊት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ቅዳሴ አስቀድሰው ከቤተክርስቲያን እንደወጡ የወገኖቻቸው ቤቶች ሲጋዩ በርቀት ቆመው በተሰበረ ልብ ሆነው ሲያነቡ እንደነበረና ከመካከላቸው የተወሰኑትን ካድሬዎች አፍሰው በቁጥጥር ሥር እንዳዋሉዋቸው ሌሎቹ ግን በጭለማ ውስጥ ተሯሩጠው እንዳመለጡ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ካድሬዎቹ ሌሊት ያሠሯቸውን ምዕመናን ከረፋዱ 4፡00 ሠዓት አካባቢ የለቀቋቸው መሆኑንም ምንጮቻችን ገልጸዋል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ከጉራ ፋርዳ በመፈናቀል አዲስ አበባ ተሰደው ከነበሩ የአማራ ተወላጆች መካከል አምስቱን የብአዴን ሰዎች ወደ ጉራ ፋርዳ ተመልሳችሁ ሂዱ ባሏቸው መሠረት ሚያዚያ 6/2004 ዓ.ም ጉራ ፋርዳ እንደደረሱ የጉራ ፋርዳ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ አቶ ጌትነት ገብረሚካኤል አዲስ አበባ የሄዳችሁት የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ለመሆን ነው በሚል በቁጥጥር ሥር ያዋሏቸው መሆኑን ታማኝ ምንጮች ለመኢአድ አስታውቀዋል፡፡

በተያያዥ ዜናም ሚያዚያ 2/2004 ዓ.ም ከደቡብ ክልል ፕሬዚዳንት ከአቶ ሽፈራው ሽጉጤ ጋር በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቀርበው <<የተፈናቀለ የለም፤ በአማሮች ላይ የደረሰ ጥቃት የለም፤>> እያሉ ሲናገሩ የተደመጡት የጉራ ፋርዳ ወረዳ የቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ መላከ ሳህል ነቢዩ ፀሃይን የ17 ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ያዘነባቸው እና ያወገዛቸው መሆኑን ከሥፍራው ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ <<ይኸ ሁሉ መከራ እና ግፍ እየደረሰብን፣ ከቤታችን እየተባረርንና በሜዳ እየተጣልን፣ በአለንጋ እየተገረፍን፣ በዱላ እየተቀጠቀጥን፣ በጦር እየተወጋን፣ ቤቶቻችን እስከ ንብረቶቻችን በእሳት እየጋዩ፣ አራሶች ከቤታቸው ተወርውረው በሜዳ እየተጣሉ፣ እመጫትና ህፃናት ሳይቀሩ ለረጅም መንገድ እርቀት ስደት እየተጋለጡ፣ እና ሌሎችም ስቃዮች እየደረሱብን ባሉበት በአሁን ወቅት መላከ ሳህል ነቢዩ ሳህል የተፈናቀለ የለም፤ ሃገሩ ሰላም ነው፤ ማንም ሰው አማራ በመሆኑ ጉዳት አልደረሰበትም፤ ማለታቸው በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖብናል>> ሲሉ ተበዳዮች ለመኢአድ የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ገልጸዋል፡፡

ህዝቡ በመላከ ሳህል ነቢዩ ፀሃይ ላይ በጣም ያዘነ በመሆኑም ሚያዚያ 5/2004 ዓ.ም. ዓርብ የሥቅለት ዕለት ቢፍቱ ሚካኤል ሄደው አገልግሎት ሊሰጡ ሲሉ ምዕመናኑ <<በፍፁም አንፈልጋቸውም እሳቸው እኛን ሸጠውናል፤ እማይወጡልን ከሆነ እኛ ቅጽረ ግቢውን ለቀን እንወጣለን>> በማለታቸው መላከ ሳህል ነቢዩ ከቤተክርስቲያን የወጡ መሆናቸው ታውቋል፡፡

ከጉራ ፋርዳ ህዝብ መፈናቀል ጋር በተያየዘም የወረዳው ባለሥልጣናት መጋቢት 29/2004 ዓ.ም. የአማራ ተወላጅ የሆኑ ነዋሪዎችን በአዳራሽ ሰብስበው <<እስካሁን ከአካባቢያችን እንዲወጡ ያደረግነው 3,000 ሰዎችን ብቻ ነው፡፡ በዕቅዳችን መሠረት 22,000 ሰዎችን እናስወጣለን፤ እስካሁን የሠራነው ግን ከአቀድነው በጣም በጣም ትንሿን ብቻ ነው፡፡>> እያሉ ከዛቻ ጋር እንደነገሯቸው ምንጮች ለመኢአድ ገልጸዋል፡፡

እንደመረጃ ምንጮቻችን አስተያየት የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ ምኒቶች አሁንም ለአማራ ተወላጆች ፍቅር ያላቸው መሆኑንና ጥላቻው፣ በደሉና ግፉ እየተፈፀመ ያለው በካድሬዎቹ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ <<ባለሥልጣኖቹ አንድ ምኒት ከአማራ ጋር ቢተባበር 7 ዓመት ይታሠራል፤ እያሉ ማስጠንቀቂያ ስለሚሠጡን ምንም ማድረግ አልቻልንም፡፡>> እያሉ ተወላጆቹ እንደሚነግሯቸው ተፈናቃዮች ይገልጻሉ፡፡

አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ከጉራ ፋርዳ የተፈናቀለ የለም ብለው ሚያዚያ 2/2004 ዓ.ም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬድዮ ከተናገሩ በኋላም የአማራ ተወላጆች በየጊዜው ቤቶቻቸው በካድሬዎች እየተቃጠሉ፣ እነሱም እየተደበደቡና በጉማሬ እየተገረፉ ከጉራ ፋርዳ እየተፈናቀሉ መሆናቸው ይታወቃል፡፡